# አዳሙ እና አለሙ ምንና ምን ናቸው?

ኢ.ተ.

ክቡራት እመ ክቡራን፤

ሰርክ አውርቼ ስለማልጠግብለት ‹‹ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ›› ላወራ ነው፡፡ በአጭሩ ለመናገር፤ ከታሪኩ ጋር ሙጭጭ ያልሁት ስለወደድሁት ነው፤ የወደድሁት ደግሞ እውነት ስለሚመስለኝ ነው፤ እውነት የሚመስለኝ ደግሞ በተለያዩ ምክኒያቶች ሲሆን ከዚህ በታች የምጽፈው አዲስ ምክኒያት ግን ከስሜት በዘለለ፤ ጠጠር ያለ ጥርጣሬ ያጭራል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በቅርቡ፤ እዚሁ ግሩፕ ላይ ፈለቀ ከበደ የተባለ ግሩም ወዳጃችን የለጠፈውንና አዳም ረታ ከአዲስ ነገር ጋዜጣ ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ አነበብሁት፡፡ በርግጥ በጊዜው ጋዜጣው ላይ ያነበብሁት ቢሆንም አሁን ግን ከዚያ በኋላ ከወጣው ‹‹ይወስዳል መንገድ፤ያመጣል መንገድ›› ጋር አናጽሬ ሳየው አስገራሚ አንቀጾችን አስተዋልሁ፡፡

ትዝ ይላችሁ እንደሆነ መጽሀፉ የወጣ ሰሞን የተወሰኑ አናቅጽ መዝገቤ እዚሁ ለጥፌው ነበር፡፡ (መለስ ብላችሁ ማየት ትችላላችሁ) እኒህን አንቀጾች ከአዳም ቃለመጠይቅ ጋር እያናጸርኩ አዳም እና አለሙ እንዴት እንደሚቀራረቡ ላሳያችሁ፡፡

**ምሳሌ አንድ-**

በቃለ-መጠይቁ ውስጥ አዳም ይህን ብሎ ነበር፤
‹‹አብዮት ሲመጣ ወይም እንዲመጣ ሲደረግ ልብ ወለድ መጽሀፍት ቢረባም ባይረባም በፓምፍሌት ተተኩ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ደስ ይል ነበር፡፡ ምክኒያቱም አዲስ ነው፡፡ (እዚህ ዘመን ላይ ቦታ ስለማይበቃን ልዝለለው እንጂ በሰፊው የምለው ኑዛዜያዊ ግለሂስ ነበር) ብዙ ሳልቆይ ሲጀመር መሰላቸቴን ያጠፋው የመሰለኝ ለአብዮት/ ለትግል ማማሟቂያ የተፈጠረው ስነ-ጽሁፍ ወደ አሰልቺ ነገር ተለወጠ፡፡››

1- ከላይ የተጠቀሰውን የቃለመጠይቅ ቃል በመጽሀፉ ካለ አንድ አንቀጽ ጋር አናጽሩት፡፡ አለሙ እንዲህ ይላል፤

‹‹. . . ከሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ወደ ሆድ ያባውን ንቃት ያወጣዋል የተሸጋገርኩት እዚህች መንገድ ጠርዝ ላይ ያለች አንዲት አልባሌ ሱቅ ጀርባ ለጥናት ክበብ ተነዝጉዤ ነው፡፡ የፓምፍሌት ደካማ ዕውቀት ከቅራሪ የቀጠነ . . . እዚህ ነው በጣቶቼ ጠቅሼ የጠባሁት፡፡ ‹ከአስተማርናችሁ አትጨምሩ አትቀንሱ› የተባልነው፡፡››

2- ልብ በሉ በቃለ መጠይቁ ውስጥ ያለው ቅንፍ የራሱ የአዳም ሲሆን ‹ኑዛዜያዊ ግለሂስ› የምትለውን ሀረግ ከይወስዳል መንገድ ጋር አናጽሩት፡፡ ‹በሰፊው የምለው አለኝ› ብሎ የተመኘው አዳም ምኞቱን በ‹‹ይወስዳል መንገድ› ማሳካቱ ይሆን? ብለን እንጠይቅ፡፡

**ምሳሌ ሁለት**

በቃለ መጠይቁ ውስጥ አዳም ይህን ብሎ ነበር፤

‹‹በሕይወቴ ብዙ ሰዎች ሲሳሳቱ አይቻለሁ፡፡ ሰዎችን ተከትዬ ተሳስቻለሁ፡፡ ቆይቼ የምረዳው ዕውነት ግን ያቺ በራሴ የስሜት ሕዋሳቶች የምረዳት ናት፡፡››

የ‹‹ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ›› ገጸ-ባህሪ አለሙ ደግሞ በመጽሀፉ ማብቂያ ግድም እንዲህ ይላል

‹‹ፊት ለፊቴ ገና የምሰርዘው ጥቁር ትዝታ አለ፡፡ አሽሙዋጣጮች እንደ ጥላ ተለጥፈው አሽከላ የሚወረውሩበትን ቀን ይጠብቃሉ . . . ‹ ድሮ ድሮ እንዲህ አልነበርክም? ድሮ ድሮ እንዲህ አላደረግክም?› የሚሉ በወንጀለኝነት አስረው ሊያቆሙኝ፡፡ እንዲህ በአራት ቃላት እጀምራለሁ፤ እንደሰው ልጅ ተሳሳትኩ፡፡

**ምሳሌ ሶስት**

በቃለ መጠይቁ ውስጥ አዳም ይህን ብሎ ነበር፤

‹‹በኃይለስላሴ አስተዳደር የወጣቶች አንዱ ባህሪ እርስ በርስ የመተማመን ነበር፡፡ የኃ/ስላሴ ፊውዳል ስርዓት ለዛን ግዜ ታዳጊ ትውልድ የሰጡት ትልቅ ካፒታል የመተማመን ካፒታል ነበር፡፡ ይሄ ስጦታ ከስድሳ ስድስታ በኋላ በመጡ ፖለቲካና ፖለቲከኞች በተለያዩ የድርጅቶች ምሕጻር ስር እየተሸነሸነ ጠፋ፡፡››

አለሙ በበኩሉ ሁኔታዎች መለዋወጣቸውን አስመልክቶ እንዲህ የሚል ብሶት ሰማል፤

‹‹አብሬያቸው ያደግሁት ሁሉ ካሱን ጨምሮ የተቀጨ ስም ዝርዝራቸውን አንብቤያለሁ፡፡ አብሮ ማደግን ፉርሽ አደረግናት፡፡ በልጅነቴ በሰበሰብኩት ዕውቀትና መታመን ገበና በማወቄ . . . ሳራን አስገድያለሁ፡፡ ካሱን አሰቅያለሁ››

‹‹እኔ ስሚን፤ እሷም ስሜን ( በጨዋታ ያደጉ ስሞቻችንን) ደም ቀብተን፣ ሬት ለቅልቀን ያጨለምነው እዚህ ነው፡፡ እኛ ነበርን? ስንወለድ ስኳር የለበሱ ልቦቻችን ጎርምሰን ስንበላላቸው እሬት ያፈሰሱት፤ በልጅነታችን መጥምጠን ጨርሰናቸው ይሆን?››

አዳም ቀጠል አድርጎም

‹‹ይህን የጠፋ ካፒታል ወደነበረበት ለመመለስ በተለያየ መልክ የተቀናበሩ የኑዛዜ ልብ ወለዶች ትልቅ ማዕከል ሆነው ማገልገል ይችሉ ነበር፡፡ ግን አልሆነም›› ይላል፡፡

አለሙ ግን ይህን ከሚያደርጉቱ አንዱ ይመስላል፡፡

‹‹ሁላችንም የየራሳችን አይነት ጎዳን አለን፡፡ ያቺ ቀይ ነቁጥ የየራሱ ቁስል ናት፡፡ ያቺ ቢጫ ነቁጥ የየራሱ ኑዛዜ ናት፡፡ የሌላውን መጋቢ መንገድ ትጠብቃለች፡፡ ጎዳናዬ ቅጠልያ ነው፡፡ *እግዚአ ተሣህለነ፡፡* ፊት ለፊቴ ገና የምሰርዘው ጥቁር ትዝታ አለ፡፡››

ይቀጥል ይሆናል፡፡